# ከመድረክ ለዴሞክራሲያዊ ምክክር በኢትዮጵያ (መድረክ)
# የተሰጠ መግለጫ

ከአንድ ዓመት በፊት መድረክ ለዴሞክራሲያዊ ምክክር በኢትዮጵያ በሚል መጠሪያ በስድስት የፖለቲካ ድርጅቶችና በሁለት ታዋቂ ግለሰቦች መቋቋሙን ለኢትዮጵያ ህዝብ ማብሰራችን ይታወሳል:: በሂደትም ሁለት የፖለቲካ ድርጅቶች ተቀላቅለውት የመድረኩ የፖለቲካ ድርጅት አባላት ወደ ስምንት ከፍ ማለቱም ይታወቃል:: የመድረኩ ዓላማ በወቅታዊ የአገራችን ጉዳዮች በመምከር በጋራ የምንስማማባቸውን የፖለቲካ አቋሞች በመለስተኛ ፕሮግራም በመቅረጽ ጠንካራ ዴሞክራሲያዊ አመራር ለመፍጠር ነበር:: ይህን ዓላማችንን ለማሳካት ወራትን ያስቆጠሩ ተከታታይ ውይይቶችን ያካሄድን ስንሆን በመጨረሻም በጋራ የምንስማማበትን የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ አንድነት መድረክ መለስተኛ ፕሮግራም ለመቅረጽና በየፓርቲዎቹ ለማጽደቅ በቅተናል::

መድረክ በጋራ ለማራመድ ከቀረፀው መለስተኛ መርሀ-ግብር በተጨማሪ የጋራ መተዳደሪያ ደንብም አጽድቋል:: በመሆኑም የጋራ የፖለቲካ ስምምነቱንና መተዳደሪያ ደንቡን መሠረት ያደረገ ቅንጅት (Coalition) ለመፍጠር መወሰናችንን ጳግሜ 3 ቀን 2001 ዓም ማመልከቻው ለብሔራዊ ምርጫ ቦርድ ጽ/ቤት አቅርበናል:: ይህን ረጅም ጊዜ ወስደን በፖለቲካ ድርጅቶች መካከል ለመቀናጀት ያደረግነው ጥረት በአገራችን ሳይሳካ ለቆየው የሕብረት ጥያቄ ምላሽ ይሰጣል ብለን እናምናለን:: በመሆኑም ድሉ የመላ አገራችን ዜጎች ነው::

መድረክ መለስተኛ ፕሮግራም ለመቅረጽ ባደረጋቸው ገንቢ ውይይቶች በበርካታ ፖለቲካዊ ጥያቄዎች ዙሪያ መግባባትን ፈጥሯል:: በተለይ እንደመነሻ በመግባብያነት የተሰማማባቸው መሠረታዊ ፖለቲካዊ ጉዳዮች ጥልቀት እንዲያገኙ በማድረግ በመለስተኛ ፕሮግራሙ ውስጥ እንዲሰፍሩ ተደርጓል:: ከነዚህ የመድረኩ አባላት ከተስማሙባቸው መሠረታዊ ፖለቲካዊ እምነቶች መካከል የሚከተሉት ይገኙባቸዋል::

መድረኩ ባዘጋጀው መለስተኛ መርሀ-ግብር ውስጥ ለኢትዮጵያ አንድነትና ሉአላዊነት መከበር በጋራ የሚቆም መሆኑንና ኢ-ፍትሀዊነትና አድሎአዊ አሠራሮች ተወግደው፤ በመከባበርና በእኩልነት ላይ የተመሠረተ አንድነት እንዲጠናከር በጽናት እንደሚሠራም ይፋ አድርጓል:: ከዚህ ሌላም የግለሰብ፤ የብሔር ብሔረሰቦች፤ ህዝቦችና የቡድን መብቶች እኩል እንዲከበሩ ሳይታክት እንደሚሰራ ገልጿል:: ሰብአዊና ዴሞክራሲያዊ መብቶች የሚከበሩበትና ማሕበራዊና ኢኮኖሚያዊ ፍትሕ የሰፈነባት፤ የበለፀገች ኢትዮጵያን ለመገንባት ያለውን ቁርጠኝነትም ይፋ አድርጓል:: በዚህ መሠረትም ሰብአዊ መብት በሁለንተናዊ መልኩ

እንዲከበር፤ ገለልተኛ የፍትሕ ሥርዓት እንዲዘረጋና የሕግ የበላይነት በተግባር እንዲገለጽና ዴሞክራሲያዊ መብቶችም ያለገደብ እንዲከበሩ በግልጽ አስቀምጧል፡፡ በተለይ በነፃ የመደራጀትና የመንቀሳቀስ መብት፤ የመናገር፤ የመፃፍና ሃሳብን በነፃነት የመግለጽ መብት እውን እንዲሆኑና ነፃና ፍትሓዊ ምርጫ በገለልተኛ የምርጫ አስፈፃሚዎች እንዲከናወን የመድብለ ፓርቲ ዴሞክራሲያዊ ሥርዓት ግንባታ እውን እንዲሆን እንደሚታገል ገልጿል፡፡

መድረክ ከዚህ በተጨማሪ በመሠረታዊ ሀገራዊ ጉዳዮች ላይ ብሔራዊ መግባባት ለመፍጠር ጥረት እንደሚያደርግና ለብሔራዊ መግባባት ከፍተኛ አስተዋጽኦ ያደርግ ዘንድ እርቅና ሠላም በአገራችን እንዲሰፍን ለማድረግ አበክሮ እንደሚጥር ይፋ አድርጓል፡፡

መድረክ የውጭ ጉዳይ ፖሊሲን አስመልክቶ ባቀረበው ሃሳብም አገራችን የባህር-በር ባለቤት እንድትሆን ለማድረግ እንደሚታገልና የሀሰብ ወደብ በሕጋዊ ዲፕሎማሲያዊና ሠላማዊ መንገድ የኢትዮጵያ አካል እንድትሆን እንደሚጥር ገልጿል፡፡

በመለስተኛ መርሀ-ግብሩ በማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ መስክም ሠፊ የፖሊሲ አማራጮችን አቅርቧል፡፡ በዚህ ረገድ አሁን መንግሥት እያራመደ ያለውን «ልማታዊ መንግሥት» ገጠርን ያማከለ የልማት አቅጣጫ ውድቅ በማድረግ በምትኩ ኢንዱስትሪ፤ ግብርናና አገልግሎት ሠጭ ዘርፎች በተመጣጠነ አግባብ የሚያድጉበትን መንገድ ቀይሷል፡፡ መሬትን በተለመከተም ገበሬው የመሬት ባለቤት የሚሆንበትን ፖሊሲ እንደሚያራምድ ይፋ በማድረግ መሬት የመንግሥትና የሕዝብ ነው በማለት ገበሬውን በገፍ የሚያፈናቅለውንና ዋስትና የማይሰጠው አካሄድ እንደሚቃወምም አስምሮበታል፡፡

መድረክ አገራችን ከገባችበት የኢኮኖሚ ቀውስጥ የምትላቀቅበትንና የዚህ ቀውስ ውጤቶች የሆኑት ሥራ አጥነትና ድህነት፤ የኑሮ ውድነት የሚወገዱበትን ፖሊሲ ተግባራዊ እንደሚያደርግም ይፋ አድርጓል፡፡ የአገራችን የትምህርት ጥራትና እድገት ፊታችን ላይ የተጋረጠውን ችግር ለመፍታት በሚያስችለው ደረጃ ስለማይገኝ በርካታና ጠንካራ ማሻሻያዎች እንደሚያስፈልጉትም በዝርዝር አስቀምጧል፡፡

በአጠቃላይ መድረክ በቅርቡ ይፋ የሚያደርገው ባለ 35 አንቀጽ መለስተኛ መርሀ-ግብር አዘጋጅቷል፡፡ መለስተኛ መርሀ-ግብሩም ለበርካታ የአገራችን ፖለቲካዊ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ጉዳዮች አማራጭ ፖሊሲዎችን አካቷል፡፡

መድረክ ያልተስማማባቸው አንዳንድ ፖለቲካዊ ጉዳዮች ቢኖሩም በስምምነት የተመዘ ገቡት የጋራ አቋሞች ብዙ ርቀት እንድንጓዝ የሚያደርጉንና የኢትዮጵያን ሕዝብ መሠረታዊ

ጥያቄዎችን ይመልሳሉ ብለን ስለምናምን በጋራ ተቀናጅተን ለመሥራት ወስነናል፡፡ ተመዝግበው ያለፉ ልዩነቶችም ቢሆኑ በሰከነና በሠለጠነ አግባብ በመያዝና ወደፊትም ለመፍታት ጥረት በማድረግ በሚያገናኙን ጉዳዮች ዙሪያ ጠንክረን ለመስራት ተስማምተናል፡፡

መድረክ እንቅስቃሴው መለስተኛ መርሀ-ግብርና መተዳደሪያ ሕገ-ደንቡን በማዘጋጀት ብቻ ሳይገድብ መጭው ምርጫ ፍትሓዊ፤ ነፃና ተአማኒ ሆኖ እንዲቀጥልም ጥረት በማድረግ ላይ ይገኛል፡፡ ሕጋዊ፤ ሠላማዊና ፍትሓዊ በሆነ መንገድ የሚደረግ ነፃ የምርጫ ውድድር በአገራችን ዘላቂ ሠላምና መረጋጋት ለማስፈን ወሳኝነት ስለአለው ለዚህም ጠንክሮ ይሰራል፡፡ በመሆኑም ከመድረኩ ምስረታ ማግስት ጀምሮ ከገዢው ፓርቲ ጋር በምርጫ ጉዳዮች ላይ ለመደራደር እንደሚፈልግ ይፋ ሲያደርግ ቆይቷል፡፡ በአካሄደው ዲፕሎማሲያዊ እንቅስቃሴዎች ሁሉ የድርድርን አስፈላጊነት ሳይገልጽ ያለፈበት ወቅት አልነበረም፡፡

መድረክ ያካሄደው የድርድር ጥያቄ በገዢው ፓርቲ በቅርቡ ተቀባይነት በማግኘቱ መድረኩም ለመደራደር ፍቃደኛ መሆኑን በመግለጽ አስፈላጊውን ምላሽ ሰጥቷል፡፡ መድረኩ ድርድር ከመጀመሩ በፊት መደራደሪያ ጉዳዮችን ለኢህአዴግ አቅርቧል፡፡ መድረኩ ለድርድር ካቀረባቸው ጉዳዮች የተወሰኑት የሚከተሉት ናቸው፡፡

ለመድረኩ እጅግ አሳሳቢ ከሆኑት ጉዳዮች አንዱ ሕገ-መንግሥታዊ ድንጋጌዎችና የሕግ የበላይነት አለመከበሩ ነው፡፡ በመሆኑም ሕገ-መንግሥታዊ ድንጋጌዎች እንዲከበሩና የሕግ የበላይነት ይረጋገጥ ዘንድ የዜጎች ሰብአዊ መብቶችና ዴሞክራሲያዊ መብቶች እንዲከበሩ ጠይቋል፡፡ በተለይ ከፖለቲካ ጋር በተገናኙ ሁኔታዎች በማሳበብ ከሕግ አግባብ ውጭ የታሠረችው ወ/ት ብርቱካን ሚደቅሳና ሌሎችም በርካታ የፖለቲካ እስረኞች የሚፈቱበትንና ዛሬም ያልቆመውና የቀጠለው በሰበብ አስባብ የሚካሄደው ጅምላ እስራት ቆሞ ዜጎች ያለምንም ገደብ ህዝባዊ ስብሰባዎች፤ ሠላማዊ ሠልፎች የሚያደርጉበት በማህበር የሚደራጅበት መብቶች የሚከበሩበት ሁኔታ ትኩረት እንዲያገኙ ተጠይቋል፡፡ ከቅርብ ዓመታት ጀምሮ ገዢው ፓርቲ በአንድ በኩል በዜጎች ላይ የሚያደርሰውን በማስገደድ አባል የመመልመልና በሌላ በኩል ደግሞ በተቃዋሚ ፖለቲካ ድርጅት አባላት ላይ የሚያደርሰው ወከባዎችና ጫናዎች እንዲቆሙ ጥያቄ ቀርቧል፡፡ የ2002 ዓም ምርጫ ፍትሓዊ ነፃና ተአማኒነት ይኖረው ዘንድ የምርጫ ቦርድና የምርጫ አስፈፃሚ አካላት ገለልተኝነት፤ የምርጫ ታዛቢዎች ገለልተኝነት፤ እንዲሁም የውጭ ታዛቢዎች መገኘት እጅግ ጠቃሚ መሆኑ በማመን በዚህ ዙሪያም ለመደራደር ሃሳብ አቅርበናል፡፡ ለምርጫ ውዝግቦች አፋጣኝ ዳኝነት የሚሰጡ ልዩ የምርጫ ጉዳይ ችሎቶች፤ የምርጫ ሥርዓትን በበላይነት የሚቃኝ (ሞኒተር የሚያደርግ) ነፃ አካል ስለሚቋቋምበትም ሁኔታ በድርድሩ እንዲካተት ጥያቄ ተጠይቋል፡፡ የመንግሥት ተቀጣሪዎች (ሠራተኞች) እንዲሁም የሕዝብ ሀብትና ንብረት ለፓርቲ የምርጫ ቅስቀሳ ዓላማ እንዳይውልም መደራደር

እንደምንፈልግ አስታወቀናል፡፡ ከዚህ በተጨማሪም ፍትሐዊ የሚዲያ አጠቃቀምና የመንግሥት የፋይናንስ ድጎማ አከፋፈል በተመለከተ ለመደራደር ሃሳብ አቅርበናል፡፡ በመድረክ በኩል ይህን ብናቀርብም ኢህአዴግ «የምርጫ ሥነ-ምግባርና ተጓዳኝ ጉዳዮች» ካልሆነ በስተቀር በነዚህ ጉዳዮች ላይ ለመወያየት መፈለጉን በግልጽ ያላስቀመጠ ከመሆኑም ባሻገር በውይይቱ አካሄድ ላይም አማራጭ የማይሰጥ አንድ ግትር አቋም በመያዙ ሂደቱን አሰናክሎታል፡፡ በኛ በኩል ግማሽ መንገድ በመጓዝ የምርጫ ሥነ-ምግባሩንና ተያያዥ ጉዳዮች ለድርድር ተቀብለን ከሌሎች ፓርቲዎች ጋር በጋራ እንድንነጋገርበትና እኛ ያቀረብናቸው ጉዳዮች ደግሞ በተጓዳኝ እንድንወያይ ሃሳብ ብናቀርብም በኢህአዴግ በኩል ተቀባይነት አላገኘንም፡፡ በመሆኑም ድርድሩ ለጊዜው ተቋርጧል፡፡

በእኛ እምነት የአገራችን ችግር መፍትሔ የሚያገኘው ገዢው ፓርቲና ተቃዋሚ ፓርቲዎች በመግባባት ሲሰሩና ሰጥቶ በመቀበል መርህ ሲንቀሳቀሱ መሆኑ እናምናለን፡፡ አሁንም ኢህአዴግ ድርድሩን ለመቀጠል ፍቃደኛ ባይሆንም በኛ በኩል ድርድሩ እንዲቀጥል ያለንን ፍላጎት ደጋግመን ለገዢው ፓርቲ የምንገልጽ መሆናችን በዚህ አጋጣሚ ሕዝብ እንዲያውቀው እንፈልጋለን፡፡ ለዚህም ዋና ምክንያት ምርጫው ፍትሓዊ፤ ነፃና ተአማኒ ሆኖ እንዲቀጥል ካለን ጽኑ ፍላጎት የተነሳ መሆኑ ለመላ ህዝባችንና ለፖለቲካ ፓርቲዎች ለመግለጽ እንወዳለን፡፡

መድረክ ከአንድ ዓመት እንቅስቃሴ በኋላ የጋራ መለስተኛ ፕሮግራም ነድፎ በአማራጭነት ለኢትዮጵያ ሕዝብ ማቅረቡ አንድ አዎንታዊ እርምጃ መሆኑን በደስታ እንገልፃለን፡፡ በዚህ አጋጣሚ መላው የአራችንን ሕዝብ ከልብ እንኳን ደስ ያላችሁ ለማለት እንወዳለን፡፡ ሆኖም አገራችን ያለችበት ውስብስብ ፖለቲካዊ ሁኔታ በተለይ ደግሞ ያለንበትን እጅግ ጠባብ ፖለቲካዊ ምህዳር ታሳቢ ስናደርግ የሚቀረን ጉዞ እጅግ ከባድ መሆኑን እንገነዘባለን፡፡ ይህን ከባዱን ጉዞ ከህዝባችን ጋር በመሆን መፍትሔ እንደምናገኝለት ግን እናምናለን፡፡ በመሆኑም በአገራችን ጠንካራ ዴሞክራሲያዊ አማራጭ እንዲኖር የሚፈልግ ዜጋ ሁሉ የተቻለውን ድጋፍ እንዲያደርግልን ጥሪያችንን በአክብሮት እናቀርባለን፡፡ እኛ በቅንጅት ብንሰባሰብም ዓላማውና ግቡ የሁላችንም ስለሆነ ለተግባራዊነቱ በጋራ መሥራት እንደሚኖርብን ለማሳሰብ እንወዳለን፡፡ በአዲሱ ዓመት ችግሮችን እየተወጣን ወደሚፈለገው ግብ ለመድረስ ሳንታክት እንደምንገሰግስ ቃል እንገባለን፡፡ ለሁላችንም መልካም አዲስ አመት ይሁንልን፡፡

| | |
|---|---|
| ኢሶዴ | አረና |
| ደኢሕዴሕ | ሶዴፓቅ |
| ኦሕኮ | ኢዴአን |
| ኦፌዴን | አንድነት |

**ኢትዮጵያ ለዘላለም ትኑር!**

**መድረክ ለዴሞክራሲያዊ ምክክር በኢትዮጵያ (መድረክ)**

**ጳግሜ 5 ቀን 2001 ዓም**

**አዲስ አበባ**